# የባሕረ ሐሳብ ቀን መቍጠሪያ መርሐ

## መግቢያ

**ይህ መርሐ ባሕረ ሐሳብ ….(1993 ዓ.ም.) ከተባለ፥ ከዶክተር ጌታቸው ኃይሌ መጽሐፍ ጋር አብሮ እንዲሄድ የተዘጋጀ ነው። እንደ ዓውደ አበቅቴ እና መጥቅዕ ያሉ ሐሳቦችን ጠለቅ ብሎ ለመመርመር መጽሐፉን ማጥናቱ ይጠቅማል። ሆኖም፥ መርሐው ለተመራማሪዎች ብቻ ሳይሆን ተራ የቀን መቍጠሪያ ለሚሹም ያገለግላል።**

**የባሕረ ሐሳብን ቀን መቍጠሪያ መርሐ ከመቀምርዎ ውስጥ እንዴት እንደሚያስገቡት በእንግሊዝኛ (ዊንዶስ የተጻፈውም የሚሠራውም በእንግሊዝኛ ነውና)፥ ከመቀምርዎ ካስገቡት በኋላ ደግሞ እንዴት እንደሚጠቀሙበት በአማርኛ እናስረዳለን።**

## Installation:

**Note:** The latest Service packs must be installed before the following installation.

I. If you download Bahra Hassab from a web page:
Let us assume that you downloded the file bh95.exe or bh98.exe into a directory called c:\temp
1. Click on Start.
2. Click on Run.
3. In the box labeled Open, type:
   C:\temp\bh95.exe (for windows 95 and windows NT)
   Or
   C:\temp\bh98.exe (for windows 98 and windows 2000)
4. Click on Ok.
   A DOS window will open and you will see white dots printed on a black background as the compressed files are being extracted.
5. When done close the DOS window.
6. Click on Start.
7. Click on Run.
8. In the box labeled Open, type:
   C:\temp\setup
9. Click on Ok.
10. Follow instructions. If you are not sure about a Yes or No question, choose Yes.

II. If your Bahra Hassab program comes on CD:
1. Insert your CD in your CD drive (e.g. D:)
2. Click on Start.
3. Click on Run.
4. In the box labeled Open, type:
   D:\win95\setup.exe (for windows 95 and windows NT)
   Or
   D:\win98\setup.exe (for windows 98 and windows 2000)
5. Click on Ok.
6. Follow instructions. If you are not sure about a Yes or No question, choose Yes.

III. If your Bahra Hassab program comes on two diskettes:
1. Insert the diskette labeled Bahra Hassab Disk 1 in the diskette drive. (e.g. A:)
2. Click on Start.
3. Click on Run.
4. In the box labeled Open, type: A:\setup.exe
5. Click on Ok.

6. Follow instructions. If you are not sure about a Yes or No question, choose Yes.
7. When asked to insert Disk #2, remove disk 1 from the drive and insert the diskette labeled Bahra Hassab Disk 2 and click on Ok.

IV. Once you have installed the program you can use it as follows.

1. Click on Start.
2. Click on Programs.
3. Click on Bahra Hassab
4. Click on Bahra Hassab for win95
   Or
   Click on Bahra Hassab for win98

**Note:** Some people reported that they could not read the Amharic text on the calander.
If you encounter such a problem do the following.

- click on start
- click on settings
- click on control pannels
- double click on fonts
- double click on a true type font called 'BH' (bh.ttf) . You should see some Amharic characters.
- close all the windows you opended.
- Try to run the Bahara Hassab program again.

## አጠቃቀም

በመጀመሪያ ከእንግሊዝኛ የተወሰዱ ቃሎችን ትርጉም እንመልከት::

| | |
|---|---|
| መርሐ | A computer program |
| መቀምር | Computer |
| መጠቆሚያ | Mouse |
| ቊልፍ | Key |
| ዊንዶስ | Windows® : የማይክሮ ሶፍት (Microsoft®) መርሐ:: |

መርሐው ሲነሣ የሚከተለውን ሰሌዳ ያሳያል::



ማስታወሻ: ከ 1 እስከ 10 የተዘረዘሩት ቊጥሮችና ቀስቶቻቸው ለማስረዳት የተጨመሩ እንጅ የመርሐው አካል አይደሉም::

ሥዕሉን እንደሚያዩት ተራ የቀን መቁጠሪያ ይመስላል:: ከተራ የቀን መቁጠሪያ የሚለይበትን ለማወቅ ከ1 እስከ 12 የተጻፈባቸውን ቁልፎች፥ መደቦችና እጀታዎች በዝርዝር እንመርምራቸው::

1 በዚህ አራት ማዕዘን መደብ ውስጥ፥ ቁጥሮች ከግራ ወደቀኝ በሚሄዱ በሁለት ረድፎች ተጽፈዋል:: የመጀመሪያው ረድፍ (1 2 3 እያለ የሚሄደው) ቀኑን በኢትዮጵያ አቆጣጠር ያመለክታል:: ከስሩ ያለው ሁለተኛው ረድፍ ደግሞ ወሩን/ቀኑን/ዓመቱን በአውሮጳ አቆጣጠር (በ ዓ.እ፥ A.D.) ያሳያል::

በቀይ ቀለም የተጻፉት መደቦች የሚያሳዩት በዓላቱ ተንቀሳቃሽ መሆናቸውን ነው:: መቀምሩ መጀመሪያ ሲነሣ፥ ከፊትዎ የሚያዩት ያሉበትን ቀን (ዛሬን) የያዘውን ሰሌዳ ነው:: "ዛሬ ም" ጀርባው ደማቅ አረንጓዴ ሆኖ ቀኖቹ በነጭ ይጻፋሉ:: ይህ ሊኾን የሚችለው የመቀምርዎ የ ውስጥ ሰዓት በትክክል የሚሠራ ከሆነ ነው:: መደቡ ሌላም ጥቅም አለው፤ በኋላ እንመለስበታለን::

2 እነዚህ ከመስከረም እስከ ጳጕሜን የተጻፈባቸው 13 እጀታዎች ናቸው:: በመቀምሩ መጠቌሚያ እ ጀታዎቹን በመጭ-ጫን የቀን መቍጠሪያውን ወራት መለዋወጥ ይችላሉ፤ ይሞክሩት:: ወሩ በተለ ወጠ ቍጥር፥ በቍጥር 9 የተመለከተውም ወር አብሮ እንደሚለዋወጥ ያስተውሉ:: ይህ የሆነበት ምክንያት፥ ሊያውቁት የፈለጉት ወር በእርግጥ መመረጡን ለማመልከት ነው::

3 መቀምርዎን መጀመሪያ ሲያስነሡ፥ ይህ መደብ በቍጥር 4 የሚነበበውን ዓመተ ምሕረት በዓመተ ዓለም ያመለክታል:: ሆኖም፥ በመጠቌሚያው ቢጫኑት እየተለዋወጠ የተለያዩ የዘመን መለኪያ ም ጥኖችን ያሳያል:: እነሱም: ዓመተ ዓለም፥ ዓመተ ሰማዕት፥ ዓመተ እስክንድር፥ መጥቅዕ፥ አበቅቴ ና ዓውደ አበቅቴ ናቸው::

ዓውደ ዓበቅቴው ሁለት ቍጥሮችን ያሳያል:: የመጀመሪያው ቍጥር ከ1-28 የሚለዋወጠው ዓውደ አበቅቴ ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ በያንዳንዱ ዓውደ አበቅቴ ውስጥ የሚገኙት 19 ዓመተ ዓውደ ዓ በቅቴዎች(ወምበሮች) ናቸው::

መጠቌሚያው ሁለት መጭ-ጫኛዎች (የቀኙና የግራ) አሉት፤ ከሁለትም በላይ ያላቸው አሉ:: ለዚህ መርሐ የሚያስፈልጉት የቀኙና የግራው ብቻ ናቸው:: ብዙውን ጊዜ የምንጠቀመው የግራው ን በመጭ-ጫን ነው:: በዚህ በቍጥር 3 መደብ ላይ ግን የቀኙን መጠቌሚያ በመጭ-ጫን ከላይ የ ተዘረዘሩትን የዘመን መለኪያዎች ወደኋላ መቀያየር ይቻላል::

4 ይህ መደብ ዓመተ ምሕረቱን ያመለክታል:: መርሐውን መጀመሪያ ሲያስነሡት፥ በዚህ መደብ ውስጥ የሚያዩት የዘንድሮውን ዓመተ ምሕረት ነው (የመቀምርዎ የውስጥ ሰዓት በትክክል የሚሠ ራ ከሆነ ማለት ነው):: ይህ መደብ ሌላም ጥቅም አለው:: መጀሪያ ቍጥር 5ን እንመልከትና እንመ ለስበታለን::

5 ቍጥር 5 ወደላይና ወደታች የሚያመለክቱ ሁለት ቀስቶች አሉት:: እነዚህን በመጠቌም (በመጭ-ጫን) ዓመተ ምሕረቱን ወደፊትና ወደኋላ ዘመን መቀያየር ይቻላል (ከዚያውም ጋር ሌሎቹም የዘ መን መለኪያዎች ይለዋወጣሉ)፤ ይሞክሩት:: ሆኖም ከ1 ዓመተ ምሕረት በታች መውረድም ሆነ ከ30ሺ ዓመተ ምሕረት በላይ መውጣት አይቻልም::

ለምሳሌ፥ 2500 ዓመተ ምሕረትን ለማጥናት ቢፈልጉ በመጠቌሚያ እየተጫኑ ለመድረስ ብዙ ጊዜ ይፈጃል፤ የቍጥር 4 መደብ ሌላው ጥቅሙ እዚህ ላይ ነው:: መጀመሪያ በመጠቌሚያው ዓመተ ም ሕረቱ የተጻፈበትን መደብ (ቍጥር 4ን) ይጭ-ጫኑት:: ቀጥሎም (የዘንድሮውን ዓመተ ምሕረት እ ንደሌለ ቈጥረው) የሚፈልጉትን ዓመተ ምሕረት ይጻፉበት:: መደቡ ውስጥ የነበረውን ዓመተ ምሕ ረት ማጥፋት አያስፈልግም:: መርሐው አዲስ ቍጥር መጻፍ ሲጀምሩ የበፊቱን አጥፍቶ በአዲሱ ይተ ካዋል:: በመጨረሻም ጽፈው መጨረስዎን መርሐው እንዲያውቅ [Enter] የሚለውን ቍልፍ ይጭ-ጫኑት::

የዚህ መደብ ቍጥር ከላይ እንደገለጽነው ዓመተ ምሕረትን ያሳያል:: አንዳንዴ ግን ዓመተ ምሕረት ን ሳይሆን ዓመተ እግዚእን መፈለግ ትሹ ይሆናል:: ለምሳሌ 1296 ዓመተ እግዚእን ለማግኘት ብ ትፈልጉ፥ አንዱ መንገድ ከ1296 ላይ 7 ዓመታት ቀንሶ 1289ን መመልከት ነው:: ወይም በቍጥር

4 የተመለከተው መደብ ውስጥ 1296ን አስገብቶ በግራው መጠቆሚያ ዓ.ም. የሚል ጽሑፍ ያለበ ትን መደብ መጭ-ጫን ነው።

6 ከ1 እስከ 532 የሚለዋወጠውን ዓውደ ቀመር ያመለክታል።
7 ከ1 እስከ 532 የሚለዋወጠውን ዓውደ ሰማዕት ያመለክታል።
8 አራቱን ወንጌላውያን ያሳያል።
9 ቍጥር 2ን ይመልከቱ።
10 ከፊትዎ የሚያዩትን ገጽ ለማተም (የወረቀት ማተሚያ ካለዎ) ይህንን ቍልፍ ይጭ-ጫኑት።
11 ስለ መርሐው ባለቤትነት ለማወቅ ይህንን ቍልፍ ይጭ-ጫኑት።

12 በዚህ አግዳሚ መሥመር ያሉ ቍልፎች የዊንዶስ (Windows®) ተጠቃሚዎች ሁሉ የሚያውቋቸው (ማወቅ ያለባቸው) ስለሆኑ ትተናቸዋል።

አሁን ወደቍጥር 1 እንመለስ።

በቍጥር 1 ከተመለከቱት መደቦች አንዱን (ባዶውን ሳይሆን ቍጥር ያለበትን) በግራው መጠቈሚያ ይጭ-ጫኑት፤ መደቡ ደማቅ ሰማያዊ ይሆናል። ከወሩ ቀኖች አንዱን መምረጥዎ ነው። ከዚያም በቍጥር 2 የሚታዩትን እጀታዎች በመጭ-ጫን ወሮቹን ይቀያይሯቸው። የመረጡት ቀን ከወር ወር ሲሸጋገሩ ደማቅ ሰማያዊነቱን አይለቅም። በቍጥር 5 የተመለከተውን ቍልፍ በመጭ-ጫን ዓመተ ምሕረቱን ቢለዋወጡም የመረጡት ቀን እንደቀለመ ይቆያል። የዚህ ጥቅሙ፥ አንድ ቀን፥ ከዘመን ወደዘመን ስንሸጋገር የሚያደርገውን ለውጥ ለመከታተል ነው። ሁለተኛም፥ አንድ (ታሪካዊ) ድርጊት፥ ከሳምንቱ ዕለታት በአንዱ፥ በወር፥ በዓመት ተመዝግቦ ብናገኝ፥ የምዝገባውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ይጠቅማል። ቀኑን መከታተል ካልፈለጉ፥ መጠቈሚያውን ቍጥር ከሌለበት ባዶ መደብ ላይ ይጭ-ጫኑት።

አንዳንድ መደቦች ውሃ ሰማያዊ አንዳንዶች ደግሞ ቢጫ ናቸው። ውሃ ሰማያዊው የሚያመለክተው ቀኑ ከቋሚ በዓላት አንዱ መሆኑን ነው። እንዲህ አይነቱን መደብ በቀኙ መጠቆሚያ ቢጫኑት ቋሚውን በዓል ያሳይዎታል። ቋሚውን በዓል ለማሳየት ሌላ ጀርባው ደማቅ ሰማያዊ፥ ጽሑፎቹ ደግሞ ቢጫ የሆኑ መስኮት ይከፈታል። ይህንን የቋሚ በዓላት መስኮት ለመዝጋት የግራውን መጠቆሚያ ይጭ-ጫኑበት።

ቢጫዎቹ መደቦች ከጀርባቸው ቋሚ በዓል ሊኖርም ላይኖርም ይችላል፤ ቋሚ በዓል ካለ በቀኙ መጠቈሚያ በመጭ-ጫን በዓሉን ማወቅ ይቻላል። ቢጫነቱ የሚያመለክተው ግን፥ በዓሉ ያ ቀን ብቻ ሳይሆን ቢጫው መደብ ያለበትን ቀን ተከትለው የሚመጡትን ቀናት (እስከ ቅዳሜ ድረስ) እንደሚጨምር ነው። ለምሳሌ ሚያዝያ 1 መደቡ ቢጫ ሆኖ በዓሉ "ስሙነ ሕማማት" መሆኑን ቢያመለክት- "ስሙነ ሕማማት" ሚያዚያ 1 ብቻ ሳይሆን ከሚያዚያ 1 እስከ ሚያዚያ 6 ያለው ሳምንት ነው።

<u>ስለ ቋሚ በዓላት፡</u>

በዚህ መርሐ ውስጥ ጠቃሚ ናቸው ብለን ያሰብናቸውን ቋሚ በዓላት አስገብተናል። ሆኖም፥ የሚወዱት ታቦት የሚነግሥበትን ቀን አያገኙት ይሆናል። የሚወዷትን ልጅዎን ልደትማ ከየት አምጥተን እናስገባዋለን? ስለዚህ፥ መርሐው ቋሚ በዓላቱን ከውጭ ፋይል እንዲያነብ አድርገናል። የውጩ ፋይል ስህተት ካለበት ወይም ጨርሶ ሊያነበው የማይችል ከሆነበት፥ የውጩን ፋይል ይተውና በልቡ የያዛቸውን ቋሚ በዓላት ይጠቀማል።

ይህ የውጭ ፋይል 'Quami.txt' ተብሎ ይጠራል። የሚገኘውም program files\bh_98_ ወይም program files\bh_95_ የተባሉ መዝገቦች ውስጥ ነው። ይህ ፋይል ስሙ እንደሚያመለክተው 'text' በመባል የሚታወቀው ፋይል አይነት መሆን አለበት። የሚጻፈውም የ "ፊደልን®" ስርዓት በሚያከብር 'Font' መሆን አለበት።

የሚከተሉት በዓላት እኛ ካስገባናቸው ጥቂቶቹ ናቸው።

0001 ልደታ
0005 አቦ (አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ)

0007 ሥላሴ
0012 ሚካኤል
1331 ጾመ ፍልሰታ /መፈቻው- ረቡዕ ወይም ዓርብ ካልዋለ ነሐሴ 16 ቀን ነው::
1343 ደብረ ታቦር (ቡሄ)
1068 አፍኒን
1321 ኡራኤል
1363 ሩፋኤል
1084 24ቱ ካህናተ ሰማይ

የአጻጻፉ ህግ ቀላል ነው:: የመጀመሪያው 4 ፊደሎች አኀዝ (ቁጥር) መሆን አለባቸው:: ከዚያ አንድ ባዶ ቦታ ትቶ የሚፈልጉት መጻፍ ነው:: የሚጻፈው ጉዳይ ግን ከአንድ መስመር መብለጥ የለበትም:: ረጅም መስመር መሆን ግን ይችላል::

የመጀመሪያው ቁጥር 0 ወይም 1 ነው:: 0 ከሆነ÷ በዓሉ ወርኀዊ ነው፤ 1 ከሆነ ደግሞ ዓመታዊ ነው:: የሚከተሉት 3 ቁጥሮች ለወርኀዊ በዓላት የወሩ ቀን (012 ሚካኤል) ÷ ለዓመታዊ በዓላት ደግሞ በዓሉ የ ሚውለት ቀን ከመስከረም 1 ጀምሮ ሲቆጠር ነው :: ለምሳሌ የዓመቱ ሥላሴ የሚከበረው ሐምሌ 7 ቀን ነው:: ሐምሌ 11ኛው ወር ስለሆነ ሐምሌ 7 የሚውለው 10x30+7=307ኛው ቀን ላይ ነው:: እንግዴህ በ ዓሉ ዓመታዊ ስለሆነ አጻጻፉ እንደሚከተለው ይሆናል::

1307 የዓመቱ ሥላሴ::

ወር በገባ 6ኛው ቀን የሚጠይቁት ሰው ካለ፤

0006 ዛሬ አቶ አረጋይን እጠይቃለሁ::

ብለው ይጽፋሉ:: የልጅዎ ልደት ጥቅምት 25 ቀን ቢሆን÷ 1x30+25=55 ነው:: ልደት ዓመታዊ በዓል ነውና አጻጻፉ እንደሚከተለው ነው::

1055 የፋጡማ ልደት::

በአንድ ቀን ከአንድ የበለጠ ጉዳይ ማስታወስ ቢሹ÷ እንደሚከተለው ማድረግ ይችላሉ::

1055 የፋጡማ ልደት:: / የከበቡሽም ልደት ነው::

ወይም::

1055 የፋጡማ ልደት::
1055 የከበቡሽ ልደት::

ባጠቃላይ 'Quami.txt' የተባለው ፋይል ውስጥ የሚከተሉትን መስመሮች ይጨምሩና ፋይሉን መልሰው ይጽፉታል:: መልሰው ሲጽፉት ግን የፋይሉ ዓይነት 'txt' የተባለው መሆኑን ያረጋግጡ::

1307 የዓመቱ ሥላሴ::
0006 ዛሬ አቶ አረጋይን እጠይቃለሁ::
1055 የፋጡማ ልደት::
1055 የከበቡሽ ልደት::

**አምኀ አስፋው**
**ጌታቸው ኃይሌ**